# የዲሲ የትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ በጨረፍታ

የዲሲ ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ በዲስትሪክቱ ውስጥ ስለሚገኙት ሁሉም የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ላይ ቤተሰቦች እንዲመለከቱ ያደርጋል። ይሄ መሳሪያ በወሳኝ ውሳኔ አሰጣጥ ማዕከል ያደረገ ከተማሪዎች ጋር ግልጽ፣ ፍትሃዊ የዲሲ ትምህርት ስርዓት የማስፈኛ መንገድ ነው።

### የትምህር ቤት ከባቢ

ስለ ትምህርት ገበታ ላይ መገኘት፣ በድጋሚ መመዝገብ፣ ደህንነት እና ሥነ ሥርዓት፣ መምህራን እና የጤና ሠራተኞች፣ እና የቅድመ ልጅነት የመማሪያ ከባቢ በተመለከተ መረጃ ያቀርባል።




### የኮከብ ደረጃ አሰጣጥ

የእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የአፈፃጸም ብቃት የሚለካው እና ደረጃ የሚሰጣው በዓመታዊው ኮከብ (የትምህርት ግልጽነት እና ዘገባ ማቅረብ) መዋቀር መሰረት ነው። ትምህርት ቤቱ አምስት ትልቁ ሆኖ ከአንድ ወደ አምስት ኮከቦች ደረጃ ይሰጠዋል።

### ከትምህርት ቤቱ መልዕክት

እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ተማሪዎቹን ለማገልገል የሚሄድባቸውን መንገዶችን፣ ለተጠቃሚዎች የትምህርት ቤቱን ልዩ ገጽታዎች ለማንጸባርቅ የሚያግዝ መልዕክት ይጽፋል።

### ያወዳድሩ

በትምህርት ቤት አፈፃጸም ብቃት፣ የሚያቀርቡት መርሀግብሮች፣ አከባቢ እና ተጨማሪ መሰረት የሚፈልጓቸውን ትምህርት ቤቶች ያወዳድሩ።

### ተዛማጅ ድርጅት መረጃ

ስለ ትምህርት ቤቱ ተዛማጅ ድርጅት በቀላሉ የሚደርስብት መረጃ።

### የተማሪ ብዛት

የትምህርት ቤቱን ጠቅላላ ተመዝጋቢ፣ ከእያንዳንዱ ዘር/ብሔር ምድብ እንዲሁም የአካለ ስንኩልነት ያለባቸው ተማሪዎች፣ እንግሊዘኛ ተማሪዎች፣ እና አደጋ ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን ጨምሮ የሌሎች ስድስት የተማሪዎች ምድቦችን ስብጥር በመቶኛ ያመላክታል።

## የዲሲ ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ ምንድን ነው?

የዲሲ ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ አንድ ትምህርት ቤት ከተማሪዎች እንዴት እንደሚሰራ እንዲያውቁ ለወላጆች ያግዛል፣ በተጨማሪም በጣም የቅርብ የሆኑ የሕዝብ መጓጓዣ መንገዶች፣ የአካዳሚ መርሀግብሮች እና ከትምህርት ውጭ ያሉ አማራጭ፣ ለወላጆች እና ቤተሰቦቻቸው ዋና የሚያገኙት ሰው፣ እና ተጨማሪ ስለ ትምህርት ቤቱ ጠቃሚ መረጃዎችን ያቀርባል። የዲሲ ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ ስለ እርስዎ ልጅ የአሁኑ ትምህርት ቤት አንዳንድ በጣም ወሳኝ ጥያቄዎች እንዲመለስልዎ ያግዞታል፣ እና ስለ ልጃቸው መወሰድ ያለባቸው ቀጣይ የትምህርት ቅደም ትከተል ለሚያስቡ ወላጆች እና ቤተሰቦች የመጀመሪያው ቅደም ተከተል ነው።

## የዲሲ ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ እንዴት እንደሚጠቀሙ?

ወላጆች ለልጆቻቸው ትክክለኛ የትምህርት ውሳኔዎች እንዲያደርጉ ከፍተኛ ጥራት ያለው መረጃ በቀላሉ ማግኘት ይፈልጋሉ እና ያስፈልጋቸዋል። ከአስተማሪ ተሞክሮ እስከ ከትምህርት በኋላ የትምህርት ቤት መርሀግብሮች እና እንቅስቃሴዎች ድረስ፣ በጣም ዘረፈ ብዙ ግብዓቶችን በመጠቀም፣ የዲሲ ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ በዲስትሪክቱ በጠቅላላ ለተማሪዎች የትምህርት ውሳኔዎችን እንዲወስኑ ለወላጆች ምርጥ የመጀመሪያ ቅደም ተከተል ይሆናል። በተጨማሪም፣ ቤተሰቦች በፍጥነት እና በቀላሉ ይሄንን መረጃ በአንድ ላይ የሚያቀናብረው ድረገጽ ላይ ሊሞሉት ይችላሉ። የዲሲ ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ ስለ ትምህርት ቤትዎ እንዲመርጡ፣ ስለ ትምህርት ቤት አፈፃጸም ብቃት ጥያቄዎችን እንዲያነሱ፣ ወይም በልጅዎ ትምህርት ቤት ቀጣዩ ቅደም ተከተል እንዲመርጡ ለቤተሰብዎ መምረጥ እንዲችሉ የሚያስችልዎ መረጃ ያቀርብሎታል። ከታች የዲሲ ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ ሊመልስልዎ የሚችለው ስለ ልጅዎ ትምህርት ቤት በተመለከተ ያለዎትን አንዳንድ ጥያቄዎች ከታች ቀርበዋል።




የዲሲ ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ የትምህርት ቤት ኮከብ ደረጃ ዝርዝሮችን ጨምሮ ስለ ዘርፈ ብዙ የትምህርት አፈፃጸም ብቃት መለያ ቦታዎች ላይ ዝርዝሮችን ያቀርባል።




የዲሲ ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ ስለ አስተማሪዎች ተሞክሮ እና የጤና ባለሙያ ሠራተኞች መኖር መረጃ ያቀርባል።




የዲሲ ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ የትምህርት ቤቱን የትምህርት መርሀግብሮች ዝርዝር እንደዚሁም የሚፈልጉትን የትምህርት መርሀግብር ዓይነት እንዲያገኙ የመፈለጊያ መሳሪያ ያቀርባል።




የዲሲ ትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ የመጓጓዣ መረጃ እና የተወሰነ አድራሻ ላይ ቅርብ የሆኑ ትምህርት ቤቶችን መፈለጊያ የካርታ መሳሪያ ያቀርባል።

## ተጨማሪ ነገር ከየት ማግኘት እችላለሁኝ?

የዲሲ የትምህርት ቤት ሪፖርት ካርድ ዲሴምበር 2018 ዓ.ም ላይ ይጀመራል። ከዲሴምበር በፊት የበለጠ ለማወቅ ይፈልጋሉ?

- ስለ ሪፖርት ካርዱ የበለጠ መረጃ ለማየት እና ስለ ወላጆች እና ቤተሰቦች OSSE የሰማው ግብረመልስ ለማወቅ osse.dc.gov/dcschoolreportcard ይጎብኙ።
- ስለ ሪፖርት ካርድ ለውጦች ለማወቅ ለመመዝገብ dcschoolreportcard@dc.gov ኢሜይል ይፃፉ።
- OSSE ን በ ትዊተር (Twitter) @OSSEDC ላይ ይከታተሉ ወይም በፌስብኩ አድራሻችን facebook.com/ossedc ላይ ያግኙን